# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ቅጽ** 33 **ቁ.**1 **ጥቅምት** 2000 **ዓ. ም**


## የት ደርሰናል?

*ግራና ቀኙን ቃኝቶ፣ ያለፈውን ከዛሬው አገናኝቶ፣ ስሜትና ፍላጎትን ሳይሆን ተጨባጩን በጥሞና መርምሮ ሁሌም ከማጠፊያው፣ ከመንታው መንገድ ሲደረስ የት ደርሰናል ማለቱና ወደየትስ መሄድ ይገባል ለሚለው ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ነው።*

*የት ደርሰናል? መከራውና ስቃዩ በዝቶብናል። ያባራል ስንል የጭቆናውና የግፉ ዶፍ ጨምሮብናል። በገዢው ክፍልና በሕዝቡ መካከል ያለው ቅራኔ ይበልጥ ከሯል። የወያኔ አገዛዝ የግንቦት 97ኡን ምርጫ ውጤት ሰርዞ፣ የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ፣ በሕገወጥ ሥልጣን ቀጥሎ የተጠላውን ከፋፋይ አገዛዙን ቀጥሎበታል። በቀን ሶስት ጊዜ ትበላላህ የተባለው ሕዝብ በቀን አንዴም በአግባቡ መብላቱ ከባድ ሆኖበታል። ስርዓቱ ሊለወጥ ቀርቶ፣ ሊሻሻል ቀርቶ፣ የለውጥን ሀሳብ ያቀነቀነን ሁሉ እያሳደደ የሚቀጣ ጨካኝና አረመኔ እንደሆነ አለ። አገዛዙ የተመሰረተበትን ሕዝብን በብሄረሰብና በሃይማኖት የመከፋፈሉ ፖለቲካ ዛሬ ብሶ ይገኛል እንጂ አለዘበም። በሃይማኖት ልዩነት ዙሪያ ደም ሲፈስም ማየት ተገደናል። የረሀብ አለንጋ ብዙ ሚሊዮኖችን ይገርፋል። ብዙ ሺ የፖለቲካ እስረኞች በየማጎሪያው ይሰቃያሉ፣ ነፃ ጋዜጦች ታፍነዋል። ፍትህ ሽታዋም ጠፍቶ ፍርደ ገምድልነት ሰፍኖ ሕዝብን መብት አልባ አድርጓል። አገዛዙ ሕዝብን በጠላትነት፣ ሕዝብም አገዛዙን በደመኛ ጠላትነት ፈርጀው እየተፋጠጡ አሉ።*

*ሁሉም በየፊናው እንዲሉ ገዢው ክፍል በነፍጥ ኃይሉ በዕብሪት የበላይ ነኝ ቢልም ባለፈው መንገድ ሊገዛ እንደማይችል መገንዘብ የግድ ሆኖበታል። በውስጡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቅራኔዎች እየተከሰቱ የአምባገነኑን ፍፁም ሥልጣን እየተጋፉ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። ከባድሜው ጦርነት በኋላ በፈነዳው ቅራኔ ህወሓት የተባለው ድርጅት ተፈረካክሶ በግለሰብና የጥቂቶች ቡድን የበላይነት ተተክቷል። በባዕድ እርዳታ አንፃር ድጋፍ*

ቢያገኝም አገዛዙ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ከሕዝብ ተነጥሎ እንዳለ  ይታያል። ገዢው ክፍል ራሱን ሊለውጥ ሆነ ሊያሻሽል ወይም መሰረቱን ሊያሰፋና ከሌሎችም ሊሰምር አልቻለም። ወጣቶችን ለመደለልና ለማሰባሰብ የተጀመረው ሰፊ ጥረት በመሰረቱ ቀውሱን የሚያረግብለት አይደለም። የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ነውና ወያኔ ከለመደበት አፋኝ ጠባዩ ሊርቅ አልቻለም። የለመደው በኃይል ረግጦ መግዛት ነውና ለችግሮች ሁሉ ቀዳሚ መፍትሄው "አምካኝ እርምጃ"ን መውሰድ ነው። ይህ ደግሞ ይበልጥ ቅራኔውን እያጎሞራው መሄዱ አልቀረም። በኦጋዴንና ሌሎች ቦታዎችም ብቅ ብቅ ያሉትና እየበዙም የመጡት ጦርነቶች ይበራከታሉ እንጂ የሚቀንሱ አይደሉም። ወደ ሶማሊያ ጦር ልኮ ወረራ ያካሄደው ይህ አገዛዝ በዚያው መቆየትም ሆነ ፈጠን ብሎ መውጣትም አቅቶት ራሱን ለባሰ ችግር አጋልጦ፥ አጋፍጦ መስጠት ተገዷል። በሁሉም መስክ ራሱን ከመጥቀም ባሻገር የሕዝብን ሁኔታ ለመለወጥና ለማሻሻል ያልቻለው ወይም ያልፈለገው አገዛዝ በግልቡ ሲታይ ጠንካራ ቢመስልም ሐቁ ግን ተዳክሞና ተቦርቡሮ መገኘቱ ደግሞ የሚካድ አይደለም። የአገዛዙ ስስ ብልቶች ለክፉ ምት ተጋልጠው ይገኛሉ። የነበረው አንድነት መላላቱ፣ በሶማሊያ ወረራው ከማይወጣበት ማጥ መግባቱ፣ ከኤርትራ ጋር ለዳግም ጦርነት ዝግጅት ማድረግ መፈለጉ፣ ማጋለጡ፣ የሕዝብን አመኔታ በባሰ ደረጃ ማጣቱ፣ አጠቃላይ ቀውሱ መብዛቱ የአገዛዙን ድክመት አጋላጭ ናቸው። በሌላ በኩል ግን አገዛዙ ለባዕድ ኃይል ተገዢ በመሆን ኢትዮጵያን በአንገብጋቢ ደረጃ የሚመለከት ጦርነት ውስጥ በመግባቱ ፀረ-ሽብርተኛ ጦርነት አውጅያለሁ ያለው ኃያል መንግስት ድጋፍን እየሰጠው ነው። በመሆኑም ይህ ኃያል መንግስት ለመለስ አገዛዝ ከሚሰጠው ድጋፍ አንዱ ፀረ ወያኔ አገዛዝ ኃይሎችን በመከፋፈልና በማዳከም መሆኑ ዛሬ ምስጢር አይደለም። ይህ የባዕድ ድጋፍ ሕዝቡ ለጠላው የወያኔ መንግሥት ሳይሆን ለሕዝቡ ቢሆንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገሪቱ እውን መሆን ቢያግዝ ለሚፈለገው ያካባቢ ሰላም የበለጠ አስተዋጽዖ እንደሚያደርግ እስካሁን ሊያዩት አልፈለጉም።

በሕዝብ ጎራ ያለውን ሁኔታ ስናይ ካለፈው የተወሳሰበ መሆኑን እንገነዘባለን። የሕዝቡ ፀረ አገዛዙ ስሜት እየጨመረና እያደገ የመጣ ሲሆን የዚህ ቁጣ ድርጅታዊ ነፀብራቅ ግን ፈዘዝ ማለቱ ይታያል። የሕዝብ ድርጅቶች በመተባበር ፈንታ ተሻክረዋል፣ በመጠናከር ፈንታ ተዳክመዋል። በሁሉም መስክ የሕዝብ የኑሮ ሁኔታ እየከፋ በመሄድ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦቱ ምርጫ ያሳየው አንድነትና ቆራጥነት ታሪካዊ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ይህን አንድነት ለማፍረስ የወያኔ አገዛዝ የሸረበው ሴራ ሁሉ ከሽፏል ማለት አይቻልም። በጅማና ሌላ ቦታዎች የተከሰተው የሃይማኖት ልዩነትን መሠረት ያደረገውና በአገዛዙ የተራገበው ግጭት በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። የመለስ ቡድን የዘረጋው የክፍፍል ወጥመድ ሁሉንም ይዟል ባንልም ወጣቶችን ሳይቀር በብሄረሰብ ደረጃ ከፋፍሎ ደም መፋሰስንም እያስከተለ

*መሆኑ ይታያል። የከተማው ነዋሪ በናጠጡ ሀብታሞችና ባረረባቸው ደሀዎች ተከፋፍሎ ቀን እየቆጠረና እየጠበቀ ያለ ሲሆን የገጠሩ ብዙሃን ደግሞ ከመቸውም ጊዜ በከፋ የስቃይ ኑሮ ውስጥ ተዘፍቆ፣ መውጫው መንገድ ተዘግቶበት፣ በመማቀቅ ላይ ነው። የኀጋዴውና አርሶ አደሩን እንቅስቃሴ በተመለከተ፥ አገዛዙ የፖለቲካ ስልጣንን ተገን አድርጎ በኤኮኖሚው መስክ የራሱን ኩባንያዎች ቅድሚያ ሰጥቶ የበላይነቱን ይዟል። የንፁህ ህብረተሰብ ነቀርሳ የሆኑት ክስተቶች ሁሉ መረን ለቀውና በገዢዎቹ ሙስናና ዋልጌነት ታጅበው ሀገርን እያጠፉ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም። የሴቶችና የህፃናት መብት በተለይ እየተረገጠ፣ ጉዲፈቻ ሽያጩ ደርቶ፣ ለዘመናዊ ባርነት ወደየአረብ ሀገሩ ማጋዙ ጨምሮ፣ የአደንዛዥ ዕፆች ልምድ ተስፋፍቶ፣ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሳይቀሩ ለሴተኛ አዳሪነት ተዳረገውና ቀሳፊው በሽታ ተስፋፍቶ ይታያል። የስነምግባርና ግብረገብ ማጠጥ በአገዛዙ እየተደገፈ ባህልና ወግ ረክሶና ተንቋሾ ባለበት፥ የዋልጌው አገዛዝ ፀረ ኢትዮጵያዊነት ዓላማ እየደራም ነው። የትምህርቱ ተቋም መደንቆርን አስቀድሞ፣ ሕዝብን ሊያገለግሉ የሚችሉት የጤና ተቋሞች ይዞታ አሳዛኝ ከመሆን አልፎ፥ ከፍቶ፣ የመንገድ አዳሪውና ስራ አጡ ቁጥር በየሳምንቱ እያደገና እየጨመረ ባለበት መርህ፥ ዓላማ፥ ሀገር ፍቅር፥ አንድነት፥ ሰብዕናን ማስከበር ወዘተ ቦታና ክብደት አይኖራቸውም። በአጠቃላይ ግን የወያኔ አገዛዝ እንደቀድሞው መግዛት እንደማይችል ሁሉ ሕዝብም እንዳለፈው ለመገዛት አለመፈለጉን አስመስክሯል።*

*ይህ የፖለቲካ ቀውስ ሁኔታ ወደ መሰረታዊ ለውጥ እንዲያመራ ከተፈለገ የሕዝቡ ጎራ የጎደለውን ድርጅታዊ ብቃት ማሳየት መቻል አለበት። ትግል ወደ ድል ሊያመራ የሚችለው በግብታዊነት ሲጓዝ ሳይሆን ተደራጅቶና ተቀናጅቶ፣ ዒላማውንና አቅጣጫውን ለይቶ ሲጓዝ በመሆኑ ድርጅት ወሳኝ ጉዳይ ነው። ድርጅቶች ራሳቸውን ድርጅት ስላሉ ወይም በፖለቲካው መስክ ስለተገኙ በእርግጥም ድርጅቶች ናቸው ማለት አይቻልም። ሕዝብን ሊያታግሉና ሊመሩ የሚችሉ ድርጅቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ፀጋ ሁሉ የሚያንፀባርቁ፣ በፖለቲካ የበሰሉ፣ ንቃተ ህሊናቸውም ቢሆን የዳበረ መሆን ይገባዋል። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ድርጅቶች ሊተባበሩና በጋራ ሊታገሉ መቻል አለባቸው። የተሰበጣጠረ ትግል የሚያስከትለው ጉዳት ግልፅ ነውናም ኅብረቱ ጠንከርና ፈርጠም ካላለ ድል የነገ ሳትሆን የሩቅ ሕልም መሆኗ አይቀርም። በዚህም መሠረት ዛሬ ከኅብረታቸው ይልቅ ክፍፍላቸው የገነነው ድርጅቶች መለስተኛ ቅራኔዎችን አስወግደው ቢቻል ለማበር ባይቻል ደግሞ ለመደጋገፍ መነሳት ይገባቸዋል። ይህ የፖለቲካ ብልህነትን ያዘለ አቅዋምና እንቅስቃሴ የሕዝብን ድጋፍ ማግኘቱ የሚያጠራጥር አይደለምና ቀነ ቀጠሮ ሳይሰጠው መሰራት ያለበት ነው።*

የሕዝብን ጎራ ለማጎልበት በሚደረገው ይህን መሰል ጥረት ላይ የሚጋረጡትንም በሚገባ ማወቁ አስፈላጊ ነው። ከዋናው ትግል አንፃር ማለትም አገዛዙን ከማስወገድ ተልዕኮ አንፃር ከዚህ አምባገነናዊ ቡድን ጋር በየትኛውም ምክንያት ሆነ ሰበብ ሊወዳጁ የሚጥሩት በዚሁ አቅዋማቸው የተነሳ ከሕዝብ ጎራ ራሳቸውን ማግለላቸው መሆኑን ሊያውቁት ይገባል ማለት ነው። አገዛዙን መጣል ሲገባ እንቀፈው የሚሉ፣ መታገል ሲገባ እናብረው የሚሉና አልፎም በመጪው ምርጫ በቧልቱ እናጅበው የሚሉ አቅዋማቸውን እስካልቀየሩ ድረስ ከሕዝብ ጎራ ወይም ከሕዝብ ድርጅቶች ወገን ናቸው ማለቱ ያስቸግራል። ስለዚህም ኅብረት ስንል ዋናውን ተልዕኮ መመሪያቸውና አቅዋማቸው ያደረጉትን ብቻ መሆኑ መሳት የለበትም። የተለጣፊ ቦታ በወያኔ አገዛዝ ፓርላማ፣ የሕዝብ ታጋይ ቦታ ደግሞ ከዚያ የራቀ መሆኑ ግልፅ ነው። አገዛዙ የተወሰኑ ተቃዋሚ ነን ብለው ግን ከጉያው ሊገቡ ያቀዱትን በአሁኑ ጊዜ ለምርጫ መዘገብኩ ሲል የተደመጠ ቢሆንም፣ ይቀየር የተባለውን የምርጫ ሕግ አልቀይርም ከማለቱ ሌላ የምርጫ ቦርዱን በራሱ ሎሌዎች መሙላቱን ሳያፍር ለፓርላማ ተብዬው ገልጧል። ይህ አገዛዝ በሁሉም መስፈርት ቢሆን አምባገነናዊ ነውና ታማኝ ተቃዋሚ የሚባለው ፅንሰ ሀሳብ በኢትዮጵያ የሚሰራ አይሆንም። ባለው ሥርዓት ያለው ምርጫ ወይ ተለጣፊ መሆን ወይም የሚሳደድ፥ የሚጠቃ ተቃዋሚ መሆን ነው። ሕጋዊ ተብለው የነበሩ ድርጅቶች ተመክሮ ይህን ሐቅ ያረጋግጣል። ለዚህም ነው ገና ድምፅ ሳይሰጥ ውጤቱ ለታወቀና ለተደመደመ ምርጫ አጃቢ ለመሆን መነሳት ከስህተትም ስህተት የሚሆነው፣ ባለፈው ምርጫ የተረሸኑትን መቶዎች ደም ረጋጭ ሆኖ የሚከሰተው።

ዓለም አቀፉና የአካባቢያችን ሁኔታ ሲቃኝም፥ ዓለም አቀፍ ፖሊስ ነኝ ባዩ ሀገር በአፍሪካ ቀንድ የሚከተለው ፖለቲካ አካባቢውን እያመሰና እያተራመሰ መሆኑ ይታያል። በፀረ ሽብርተኛ ጦርነት ሽፋን ለአምባገነኖች ድጋፍን እየሰጠ በሕዝብ መብት ላይ ለሚፈፀሙ በደሎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብሏል። ተባብሶ የሚገኘው የምስቅልቅልና የጦርነት ሁኔታም በሶማሊያ ላይ በተካሄደው ወረራ ሊረግብ ቀርቶ ተባብሶ መገኘቱ በዓለም ዘንድ የታወቀ ነው። በአገዛዙና በሻዕቢያ መሀል ያለው ሊያገረሽ የደረሰው ጦርነት በአሁኑ ወቅት በእጅ አዙር በሶማሊያም በኦጋዴንም ወዘተ እየተካሄደና ዕልቂትንም እያስከተለ ነው። የሶማሊያ ጦርነት፣ የሱዳን የደቡቡ የሰላም ስምምነት መዛነፉ፣ በዳርፉር ውጊያው አለማቆሙ፣ በሶማሊያም ሆነ በሱዳን የዘይት/ቤንዚን ጉዳይ ለችግሮች አንዱ መንስዔ መሆኑ ወዘተ ይህ አካባቢ ዛሬም ወደ ከፋ ቀውስ እያመራ መሆኑን ይጠቁመናል። በአካባቢው ጣልቃ የገባው ኃያል መንግሥት ለመለስ ዜናዊ አገልጋይ የሚሆን ፀረ-ሽምቅ ተዋጊ ጦር ከማሰልጠኑ ሌላ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መረጃዎችንም እንደሚያቀብለው መለስ ራሱ የገለጠውና ያመነው ጉዳይ ነው። የመለስ ወራሪ ጦር በሶማሊያ መግባቱና አክራሪ የአካባቢ ኃይሎችም ከሶማሊያ ሽምቅ ተዋጊዎች ጎን መቆማቸው፣ በአባይ ውኃ ምንጭነቷ የተነሳ

ኢትዮጵያን በመጥፎ የሚያዩ ሀገሮችም በዚሁ መግባታቸው ለችግሩ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ማጠየቂያዎችን ሰጥቶ መዘዙን ማጠናከሩ ግልፅ ሆኗል፡፡ በአባይ ውኃ አጠቃቀም ላይም፥ በበረሀ ብዙ ሚሊዮን ዜጋዋን ማስፈር የፈለገችው ግብፅ ተጨማሪ ውኃ እየጠየቀች ባለችበት፣ ሕዝባችን በምድሩ የተከማቹና የሚፈሱ ወንዞችን ተጠቅሞ የረሃብ ምሳሌና መሳለቂያ ከቶም እንዳይሆን አጥብቆ በሚፈልግበት ሁኔታ ነገ ወደ ጦርነት ሊያመራ እንደሚችል የሚገመት ነው፡፡ ያለው የአካባቢያችን ሁኔታ ውጥንቅጥ ለኢትዮጵያ ህልውና አደጋን አዘል ቢሆንም በስልትና ዘዴ ከተያዘ ደግሞ ለትግሉም የሚጠቅም ሊሆን እንደሚችል ይታያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ግን በሕዝብ ደረጃ ታውቆ ማከሚያው ሊፈለግለት የሚገባው ደግሞ በአገዛዙም በባዕዳኑም የተሸረበውን ሴራን የሚመለከት ነው፡፡ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ኃይሎችን ለመነጠልና ለማጥቃት የታቀደው በስራ እየዋለ ነው፡፡ ይህ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የተመደበለት ሴራ በልዩ ልዩ መንገድ እየተሰራ ያለው የተወሰኑ ድርጅቶችን በዒላማ አስገብቶ ነው፡፡ የተባሉትን ድርጅቶች ለማጥላላት፣ ከሕዝብ ለመነጠልና አልፎም ለማዳከም በይፋና በረቀቀም መንገድ ዘመቻው ተጀምሮ እየተካሄደ ነው፡፡ የድርጅቶች ቀውስ የራሱ ውስጣዊ ምክንያት ቢኖረውም የወያኔ አገዛዝና የባዕዳን ኃይሎች እጃቸው የለበትም ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህም ሕዝብ የዚህን ሂደት ይዘት አውቆ ሴራውን ለማክሸፍ መረባረብ ይኖርበታል፡፡ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ኃይሎችን መንከባከብ፣ የእንክርዳዱን ማንነት ማወቅ፣ ማጋለጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ሀገርን አሳልፎ ያለመስጠትን፣ በሕዝባዊ ቃል ኪዳን ፀንቶ መገኘትን ፖለቲካን ያለማወቅ አድርገው ሊፈርጁ የተነሱ ቢኖሩም፥ ሀገር ወዳድ ፖለቲካና አቅዋም መቸም ቢሆን መች ለወያኔ አገዛዝ አለመንበርከክን መርህ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

የደረሰንበት የተባባሰ ቀውስ ሁኔታ የሚያመለክተን ቀውሱ ዘርፈ ብዙ ሆኖና ተወሳስቦ ይበልጥ ሊባባስ እንደሚችል ነው፡፡ በአገዛዙ የተጠመደው የብሄረሰብና የሃይማኖት ልዩነት ፈንጂ ሀገሪቷን ለከፋ ሶማሌን መሰል ብጥብጥና ጦርነት ሊዳርጋት የሚችልበት ሂደት የለም ማለት አይቻልም፡፡ የመለስ ቡድን ኢትዮጵያን ለከፋ አደጋ አጋልጦ ባወጣው ያውጣው አጥፊነት ከተሰማራ የቆየ ነውናም ይህ ርኩስ ዓላማው ፍሬ እንዳያገኝ መታገሉ የግድ ነው፡፡ ከውስጥም ከውጪም በሀገሪቷ ላይ የተዘጋጀውን መዘዘኛ ጥቃት ለማጨናገፍ ደግሞ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በስልትም መታገልን ይጠይቃል፡፡ ያለንበት ወሳኝ የታሪክ ጊዜና ቦታ የነገው የሀገራችንን ዕጣ ከመወሰን አንፃር ብልህ እና አርቆ ተመልካች ሆነን መውሰድ ያለብንን እርምጃዎች ይጠቁመናል፡፡ ለከፋፋዩ አገዛዝ ሰለባ በመሆን በብሄረሰብና በሃይማኖት ተከፋፍለን ሀገራችንን ለቅርጫ ከዳረግናት ራሳችን በራሳችን ሀገር አልባ መሆናችንን በላያችን ላይ እናመጣለን ማለት ነው፡፡ በተቃራኒው ግን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ

በሚገባ በማጤን፣ ከፋፋይ ሴራዎችን በማጨናገፍ፣ ኅብረታችንን በማጠንከር፣ ከተሳሳተ ፖለቲካና ለአገዛዙ አስጎንባሽ መንገዶችና ውሳኔዎች በመራቅ ቆርጠን ከታገልን ሀገሪቷን ነፃ ለማድረግ አቅምና ዕድል ይኖረናል፡፡

የወያኔ አገዛዝ ጦሩን በብሄረሰብ ደረጃ ከፋፍሎና በተለይም የትግራይ መኮንኖችን በሹመትና ጥቅማ ጥቅም ከጎኑ አሰልፎ የአፈና ክንዱን በማፈርጠም ማንኛውንም ተቃውሞ ለማሽነፍ ይመኛል፡፡ በንዋይና በሌላም መንገድ በርካታ ዜጋን ለመደለልም መነሳቱን የሚሌኒየሙ ጋጋታ ያሳየው ነው፡፡ በመሆኑም ጥያቄው የትኛው ዜጋ በሆዱ ያስባል፣ የትኛው ዜጋ ሀገሩን ያስቀድማል ሆኖ ይገኛል፡፡ ወታደሩና ሠራዊቱ ለሀገር ይቆማል ወይስ የአረመኔው ቡድን መሳሪያ ይሆናል የሚለውም ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ወጣቱ ትውልድስ ያለፈውን የታጋይ ወጣቶች ታሪክ በግንቦተ 97 አድሶ ሊቀጥል ያሳየውን ቁርጠኝነት ይዞ ይቀጥላል ወይስ ስደትን ይመርጣል ወይስ ለወያኔ አገዛዝ ድለላና ክፍፍል ሰለባ ይሆናል የሚለውንም አንገብጋቢ ጥያቄ ምላሽን ፈላጊ ሆኗል፡፡ ሁለገቡንስ ትግል ከግብ ለማድረስ ምን ዓይነት የፖለቲካ ስልትን ተከትሎና አጋሮችን አብዝቶ መገኘት ያሻል፡፡ የባዕዳኑን ሴራ ለማክሸፍና በሕዝባችን አቸናፊነት ላይ ተማምኖ ወደ ድል ለመጓዝ ምን ምን መደረግ አለበት ብሎም መጠየቂያና ምላሽ ማግኛ ጊዜ ነው፡፡ በህብረት ለመታገል ህብረትን ማጠናከር፣ ክፍፍልን በየፈርጁ ማስወገድ፣ የወያኔ አገዛዝ ዋነኛ የሕዝብ ጠላት መሆኑን ማስረገጥ፣ መሰባሰብ መደራጀት፣ የትግሉን ምስጢር መጠበቅ፣ ሠራዊቱ ወደ ሕዝብ ፊቱን እንዲመልስ፥ ከሕዝብ ጎን እንዲሰለፍ መቀስቀስ፣ የጠላትን ጎራ መከፋፈል፣ ለአድማ በስልት መዘጋጀት፣ መደራጀትና ሀቀኛ የህዘብ ድርጅቶችን መደገፍ… ወዘተ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያን ማዳን የሚችለውና የሚገባውም የሀገሪቷ ዜጋ ነውና ኢሕአፓ ሀገር ወዳድ ዜጋው ሁሉ ለወሳኝ ትግል በኅብረት እንዲነሳ ዳግም ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊ ነው!!!